# የህክምና አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 667/2013

Medical Service Provision Directive No. 667/2013

የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን
Ethiopian Civil Aviation Authority

ግንቦት 1፥ 2011

## መግቢያ

ባለስልጣን መ/ቤቱ በአዋጅ ከተሰጠው ከፍተኛ ሀገራዊ ኃላፊነት አኳያ ዓለምአቀፍ ህግጋት፣ ደንብና ተቀባይት ያላቸውን መመሪያዎች ጠብቆ (SRPs) የመስራት ግዴታ አለበት፡፡ በአዋጅ ከተሰጠው ኃላፊነት አንዱ ከአደጋና ከስጋት ነፃ የሆነ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት ሲሆን ይህንን አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎች ከሥራው ባህሪ አንፃር በየጊዜው የጤንነት ምርመራ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ባለስልጣን መ/ቤቱ የዓለምአቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ባወጣው መስፈርትም ሆነ ከሙያው ጋር ተያያዥ በሆነ መመሪያ መሠረት በየአራት ዓመቱ የጤንነት ሁኔታ ማስመርመርና በኦዲት ወቅትም የባሙያዎቹን የጤንነት ሁኔታ ማረጋገጫ ማስረጃ የማቅረብ ዓለምአቀፍ ግዴታ ነው፡፡ በኦፕሬሽንና ቴክኒካል ሥራ ሂደት ላይ የሚቀጠሩ አዳዲስ ሠራተኞችንም አሰልጥኖ ለመቅጠር በቅድሚያ የጤንነት ምርመራ የሚደረገው ራሱን የቻለ የአቪዬሽን ሜዲካል አሴሰር ባለበት የጤና ተቋም ብቻ ነው፡፡

ባለስልጣን መ/ቤቱ ከዓለምአቀፍ ግዴታ ከመወጣት ባሻገር የአቪዬሽን ዘርፍ እድገት ለማስቀጠል የሠራተኞችን ደህንነትና ጤንነት የመጠበቅና ምቹ የሥራ አካባቢን የመፍጠር ኃላፊነት አለበት፡፡ ባለስልጣን መ/ቤቱ ይህንን ለመፈፀም የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ በመሆኑም አገልግሎት አሰጣጡን በመመሪያ በማስደገፍ ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ በባስልጣን መ/ቤቱ ባለው መካከለኛ ክሊኒክና ከሌሎች የጤና ተቋማት ጋር የአገልግሎት ስምምነት ውል በመግባት እየተሰጠ ይገኛል፡፡ ሆኖም ካለው ነባራዊ ሁኔታ በመመሪያው የተካተቱት አንቀፆች ይዘት በርካታ ክፍተቶችና ችግሮች ያሉበት በመሆኑ ለአፈፃፀም ሆነ ለክትትል አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡

ስለሆነም የህክምናው አገልግሎት ጥራትና ተደራሽነት ያለው እንዲሆን፣ ለህክምና የተመደበው በጀት ኢኮኖሚያዊ/የገንዘብ ምጣኔን ባገናዘበ መልኩ ለመጠቀምና በአፈፃፀም ሂደት ያሉትን ክፍተቶችን በመለየት እርምጃ ለመውሰድ እንዲቻል መመሪያውን ፈትሾ ማስተካከል ተገቢ ከመሆኑም በላይ በኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን መቋቋሚያ አዋጅ 616/2001 አንቀጽ 92/2 መሠረት ባለስልጣን መ/ቤቱ መመሪያ የማውጣት ስልጣን ስለተሰጠው ሥራ ላይ የነበረውን መመሪያ ለመተካት የወጣ አዲስ መመሪያ ነው፡፡

### የመመሪያው ዓላማ

የህክምና አገልግሎት አሰጣጥ መሜያ ግልፅና ለአፈፃፀም ምቹ በሚድረግ፣ በተቋሙ ክሊኒክ እየተሰጠ ያለውን የህክምና ሽፋን በማሻሻል የተገልጋዩን እንግልት ለማስቀረት የሚያስችል በባለሙያን የታገዘ አሰራርን ለማዘርጋት፣ ተቋሙ ለህክምና የሚያወለው በጀት ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ ለማጠቀም በሚያስችልእና ተጠያቂነት ያለበት አሰራርን ለማስፈን፣ የተሰጠውን አገልግሎት አፈፃፀም ለመከታተልና ለመቆጣጠር፣ የጤና ተቋማቱ እየሰጡ ባለው አገልግሎት የክትትል (Supervision) ሥራ በማከናወን የተሻለ አገልግሎት ለሰጡ የሚችሉ የህክምና ተቋማትን በህጋዊ መንገድ ስምምነት በሚፈፀም ጥራትና ተደራሽ ያለው አገልግሎት ተገልጋዩ እንዲያገኝ በሚድረግ የሠራተኛውን ደህንነትና ጤንነት በማጠበቅ ምቹ የሥራ አካባቢን መፍጠር ነው፡፡

## 2.አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን የህክምና አገልግሎት አሰጣጥ የአሰራር መመሪያ ቁጥር 667/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጠቀሱት፡ -

3.1 «ባለስልጣን መ/ቤቱ» ማለት የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን ነው፡፡

3.2 "ተገልጋይ" ማለት በባለስልጣን መ/ቤቱ በቋሚነት/በኮንትራት የተቀጠረ ባለሙያ/ ሠራተኛ ነው፡፡

3.3 "የአሰራር መመሪያ" ማለት የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን የህክምና አገልግሎት አሰጣጥ አሰራር መመሪያ ነው፡፡

3.4 "የህክምና ተቋማት" ማለት ባለስልጣን መ/ቤቱ በግዥ ህግና መመሪያ መሠረት በግልፅ ጨረታ በማወዳደር ብቃትና ጥራት ያለው አገልግሎት ከሚሰጡ የመንግስት ወይም ከተመረጡ የግል ሆስፒታሎች፣ ፋርማሲዎች፣ የህክምና ምርመራ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት (Diagnosing Centers) እና ጤና ጣቢያ የወል ስምምነት የሚፈፀምባቸው ህጋዊ ተቋማት ናቸው፡፡

3.5 "ድንገተኛ ህመም" ማለት አስቸኳይ የህክምና አገልግሎት የሚያስፈልገው፣ ጊዜ የማይሰጥና ታማሚውን በፍጥነት የህክምና እርዳታ ካላገኘ ለከፋ ጉዳት የሚዳርግ ህመም ማለት ነው፡፡

3.6 "አዲስ ምልምል ሠራተኛ" ማለት በተቋሙ በአየር ትራፊክ ተቆጣጣሪነት፣ በኮምኒኬሽን፣ ናቪጌሽንና ሰርቬለንስና በኤሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ስልጠና በመውሰድ በቋሚነት የሚቀጠር ባለሙያ ነው፡፡

3.7 "የሙከራ ጊዜ ሠራተኛ" ማለት አዲስ የተቀጠረና በሙከራ ጊዜ ላይ ያለ ሠራተኛ ማለት ነው፡፡

3.8 "የኮንትራት ሠራተኛ" ማለት ለተወሰነ ጊዜ ዘላቂነት በሌለው ሥራ ላይ ለስድስት ወራት ወይም እስከ አንድ ዓመት ድረስ በወል በሚታደስ ስምምነት የሚቀጠር ሆኖ የኤርክሩ ሜምበሮችን አይመለከትም፡፡

3.9 «አደጋ» ማለት ተገልጋዩ በሥራ ላይ እያለ ከሥራው ጋር የተያያዘ አደጋ ማለት ነው፡፡

3.10«ሕመም» ማለት በቋሚነት/በኮንትራት ተቀጥሮ የሚያገለግል ሠራተኛ በተለያየ ምክንያት በጤንነቱ የሚያጋጥመው እክል ማለት ነው፡፡

### አንቀፅ -1

### የህክምና አገልግሎት አሰጣጥ

1.1. በባለስልጣን መ/ቤቱ በቋሚነት/በኮንትራት የተቀጠረ ሠራተኛ/ኃላፊ ህመም ሲያጋጥመው በሥራ ክፍል ኃላፊ/የቅርብ ኃላፊ በአውቶሜሽን ሲስተም በተቋሙ ክሊኒክ አገልግሎቱን ያገኛል፣

1.2. በቋሚነት/በኮንትራት የተቀጠረ ሠራተኛ/ኃላፊ ያጋጠመው ህመም በክሊኒክ ደረጃ ሊታከም የማይችል መሆኑ በክሊኒኩ የጤና ባለሙያዎች ተረጋግጦ የተሻለ ህክምና ሊያገኝ ወደ ሚችልበት የጤና ተቋም የሪፈራል ማስረጃ በመያዝ አገልግሎቱን ያገኛል፣

1.3. ከላይ በአንቀጽ 1/1.2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ ደንበኛው ህክምና ተቋም ሠራተኞች የሚሄዱት ሠራተኛው ያጋጠመው ህመም ከክሊኒኩ አቅም በላይ ብቻ መሆኑ ሲረጋገጥ እንጂ እንደመብት ተወስዶ የሚጠየቅ ያለመሆኑ፣

1.4. ተገልጋዩ የተሰጠው የሪፈራል ወረቀት የሚያገለግለው ለአንዴ ህክምና ብቻ ሆኖ ተከታታይ ህክምና ወይም ተጨማሪ ምርመራ እንዳለው ማስረጃ ሲያቀርብ ወይም በሌላ ሐኪም መታየት እንዳለበት ቀድሞ ባየው ሀኪም

ሲታዘዝና ማስረጃ ሲያቀርብ ብቻ በድጋሚ የሪፈራል ወረቀት በማዝ ወደ ደንበኛው ክሊኒክ በሜድ አገልግሎቱን ያገኛል፣

1.5. ታካሚው በህክምና ተቋሙ ለተጨማሪ ምርመራ ወይም ተከታታይ ህክምናና ክትትል ቀጠሮ ከተሰጠው የቀጠሮውን ህጋዊ ማስረጃ ወደ ተቋሙ ክሊኒክ በመቅረብ የሪፈራል ማስረጃ በማዝ ህክምና አገልግሎቱን ያገኛል፣

1.6. አንድ ተገልጋይ ደንበኛ ባልሆነ የህክምና ተቋምና በመንግስት ሆስፒታል ተከታታይ ህክምናና ክትትል የሚያደርገው በደንበኛ የህክምና ተቋም ሪፈር ሲባልና አገልግሎቱ በሌሎች ደንበኛ የህክምና ተቋሞች የማይገኝ ሲሆን ብቻ ነው፣

1.7. ተገልጋዩ በደምበኛ የህክምና ተቋም ማግኘት የሚችለው የህክምና አገልግሎት የክሊኒክ ባለሙያው በሪፈራሉ ላይ ከህመሙ ጋር በተያያዘ በተገለፀው የስፔሻሊቲ ዓይነት ብቻ ሲሆን በአንዴ በተላከበት በዚያው በሌላ ሐኪም/ስፔሻሊቲ ማሳየትም ሆነ ማሳከም አይቻልም፤ ይሁን እንጅ ከህመሙ አጣዳፊነት የተነሳ ቀደሞ ያየው ሐኪም በሌላ ሐኪም ማሳየት እንዳለበት በህክምና ተቋሙ ወደ ተፈለገው ስፔሻሊቲ ሲልከው በዚያው ማሳየት/ማሳከም ይችላል፣

1.8. ተገልጋዩ ባለስልጣን መ/ቤቱ ስምምነት ከፈፀማቸው የጤና ተቋማት የህክምና አገልግሎቱን ማግኘት የሚችሉት ከስራ ሰዓት ውጪና በበዓላት ቀናት በሚያጋጥም ድንገተኛ ህመም ካልሆነ በስተቀር በመደበኛ የሥራ ሰዓት የክሊኒኩ የህክምና ባለሙያ ሚጋገጫ ሲሰጥ ብቻ ነው፣

1.9. በአንቀፅ 1/1.7 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በአዳር ሽፍት የሚሰሩ ሠራተኞች በሥራ ላይ እያሉ ለሚያጋጥማቸው ህመም የባለስልጣን መ/ቤቱ ክሊኒክ የ24 ሰዓት አገልግሎት ስለማይሰጥ ከሥራ ሰዓት ወጪ ለሚያጋጥም ህመምና አደጋ ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ እንደአደጋውና እንደህመሙ አጣዳፊነት ቢቻል ውል በፈፀሙበት የህክምና ተቋም ካልሆነ አቅራቢያ ከሚገኝ የህክምና ተቋም አገልግሎቱን ማግኘት ይችላሉ፣

1.10. በደንበኛ የጤና ተቋም ህክምና እንዲያገኙ የተወሰነላቸው ተገልጋዩች ከባለስልጣን መ/ቤቱ ክሊኒክ የክሬዲት ማጠየቂያ ደብዳቤ እና ሪፈር በመውሰድ አገልግሎቱን ማግኘት ይችላሉ፣

1.11. በባለስልጣን መ/ቤቱ ሁለት ዓመትና በላይ ያገለገሉ ሠራተኞች የዓይን ሕክምና ሲያደርጉ በህክምናው ወጤቱ መሠረት ለሚታዘዝ መነፅርና ለፍሬም መግዣ 700.00 (ሰባት መቶ) እንዲሁም ለሌንስ መግዣ እንደቁጥሩ ብር 600.00 (ስድስት መቶ ) በድምሩ ከ1,300.00 (አንድ ሺ ሶስት መቶ ብር) ያልበለጠ ወጪ በባለስልጣን መ/ቤቱ ይሸፈናል፤ ሆኖም ለፍሬም መግዣ የሚከፈለው ለአንድ ጊዜ ብቻ ነው፣ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ተገልጋዩ የታዘዘለት መነፅር ስድስት ዓመት የሞላው ከሆነና በሀኪም የመነፅር ማዘዣ ተያይዞ ሲቀርብ የመነፅር ዋጋው ሙሉ ይሸፈናል፣

1.12. የእይታ መነጽር (Sight Mirror) ለሚጠቀሙ የሌንስ ዓይነቱና ቁጥሩ የመቀየሩ አስፈላጊነት በዓይን ሐኪም ስፔሻሊስት በታዘዘው የህክምና ሚጋገጫ መሠረት በየሁለት □መቱ ለሌንስ በመሚያው የተገለፀው ሙሉ ወጪ በባለስልጣኑ መ/ቤት ይሸፈናል፡፡፣ሆኖም ካጠቃቀምና ከአያያዝ ጉድለት የተሰበረ ወይም የጠፉ መነፅር ወጪ በባስልጣን መ/ቤቱ አይሸፈንም፣

1.13. ተገልጋዩ የጥርስ ህመም ሲያጋጥመው ውል በተገባበት የጤና ተቋም የጥርስ ህክምና፣ መጥርቦርን ለማስደፈንና የተበላሸን ጥርስ ለማስነቀል ሙሉ ወጪው ይሸፈናል፤ ሆኖም ጥርስን ኬሚካል ማስጠብ እንዲሁም በተለያየ ምክንያት ማለትም ከሥራ ጋር ባልተያያዘ የተነቀለ ጥርስ የሚተከል ወጪ በባለስልጣን መ/ቤቱ አይሸፈንም፣

1.14. አንቀፅ 1/1.13 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በሥራ ላይ በሚደርስ አደጋ ተገልጋዩ የጥርስ መውለቅ ወይም መሸረፍ አደጋ ሲያጋጥም ለሠራተኛው ወል በተገባለት የጤና ተቋም በባለስልጣን መ/ቤቱ ወጪ እንዲታከምና ጥርሱ እንዲተከል ይደረጋል፣

1.15. የጆሮ ህመም ያጋጠመው ቋሚ ሠራተኛ በደንበኛው ክሊኒክ የህክምና ወጪው ተሸፈኖ እንዲታከም ይደረጋል፣

1.16. አንቀፅ 1/1.15 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ቋሚ ሠራተኛው በሥራ ምክንያት ዘለቄታዊ የሆነ የመስማት ችግር ሲያጋጥመውና ይኸው በህክምና ባለሙያ ሲረጋገጥ የማዳመጫ መሣሪያ ለአንድ ጊዜ ብቻ ሙሉ ወጪው ተሸፍኖ ለሠራተኛው ይሰጣል፣

1.17. በባስልጣኑ መ/ቤት የተቀጠረች ሠራተኛ የቅድሙ-ወሊድ ምርመራ ክትትል በክሊኒኩ ባለሙያዎች እንድታገኝ ይደረጋል፤ ሆኖም ግን ከወሊድ ጋር በተያያዘ የሚጠየን የህክምና አገልግሎት እና እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ክትትሎችን ሙሉ ወጪ ተሸፍኖ በደንበኛ የጤና ተቋም እንድታገኝ ይደረጋል፣

1.18. አንቀፅ 1/1.17 እንደተጠበቀ ሆኖ ተገልጋይ ነፍሰጡር ሠራተኛ በድንገተኛ ወሊድ ወይም ባጋጠማት የእርግዝና ችግር ምክንያት /complication/ በድንገተኛ ሁደበኛ ባልሆነ የመንግስት/የግል የጤና ተቋም ሲያዋልዷት የወሊድ አገልግሎት ካገኘች የወሊድና ተዛማጅ ወጪዎች እስከ ብር 4,000.00 (አራት ሺ ብር) በቀረበው ደረሰኝ መሠረት በባስልጣኑ መ/ቤት ይሸፈናል፡፡ የወሊድ አገልግሎቱን በመንግስት የህክምና ተቋም ካገኘች ያወጣችው ሙሉ ወጪ ይሸፈንላታል፤ ሆኖም ከዚሁ ጋር በተያያዘ የሚታዘዝ መድሃኒት ከቀዶ ጥገና ጋር ግንኙነት ከሌለው በስተቀር ግዥው ከደንበኛ መድሃኒት ቤት ይሆናል፣ መድሃኒቱ ከደንበኛው መድሃኒትቤት ካልገኘ ያለመገኘቱን ከሁለት ደንበኛ መድሃኒትቤት ሚረጋገጫ በማቅረብ ከሌላ መድሃኒትቤት በመግዛት ወጪ እንዲተካ ይደረጋል፣

1.19. በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 48/6 መሠረት ባለስልጣን መ/ቤቱ ከአንድ ዓመት በታች ህፃን ላላቸው ሴት ሠራተኞች የህፃናት ማቆያ በማዘጋጀትና ባለሙያ በመቅጠር አገልግሎቱን ይሰጣል፣ ሆኖም ተቀጣሪ ሴት ሠራተኞች ምንያህል ጊዜ ከልጆቻቸው ጋር እንደሚቆዩ ሰልፉና የህፃናት ማቆያ አሰራርና አደረጃጀት ወደ ፊት በመንግስት በሚወጣው ወጥ መመሪያ መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፣

1.20. በህፃናት ማቆያ የሚውል ህፃን የጤንነት እክል ሲያጋጥም የመጀመሪያ እርዳታ በክሊኒኩ ባሉ ባለሙያዎች ብቻ ይሰጣል፣

1.21. ከአንድ ዓመት በታች ልጅ ያላቸው ሴት ሠራተኞች ልጇን/ቷን ለማሳከም የቀሩበት ጊዜ የህክምና ማስረጃ ሲያቀርቡ በህመም ፈቃድ ይያዝል፣

1.22. በባለስልጣን መ/ቤቱ የተቀጠሩ ሠራተኞች ወል በተገባው የህክምና ተቋም ተኝተው መታከም የሚችሉት ለ30 ቀናት ብቻ ሆኖ ባለስልጣን መ/ቤቱ የሀያ ቀናቱን ሙሉ ወጪ እንዲሁም የ10 ቀናቱን 50% ብቻ የህክምና ወጪ ይሸፈናል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ከህመሙ ጋር በተያያዘ ከላይ ከተጠቀሰት ቀናት በላይ ተኝቶ ለሚታከም ታካሚ ወጪው በባለስልጣን መ/ቤቱ አይሸፈንም፡

1.23. ሆኖም ከላይ በአንቀጽ 1/1.22 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ህመሙ ካደረሰበት ጉዳት አንፃር ተገልጋዩ ከሆስፒታል መውጣቱ ለህይወቱ አስጊ ሆኖ ከተገኘና በህክምና ባለሙያ በማስረጃ ተደግፎ ሲገለፅ ከአንድ ወር በላይ እስከ ሶስት ወራት ለሚደርስ ጊዜ በደንበኛው የህክምና ተቋም ብቻ የሚተኛ ታካሚ ወጪው በባለስልጣን መ/ቤቱ ሊሸፈን የሚችለው 50% አንድ በጀት ዓመት ለአንድ ጊዜ ብቻ ይሆናል፣

1.24. በባለስልጣን መ/ቤቱ የተቀጠሩ ሠራተኞች በመንግስት የህክምና ተቋም ተኝተው መታከም የሚችሉት ለ30 ቀናት ብቻ ሆኖ ባለስልጣን መ/ቤቱ የ30 ቀናት የህክምና ወጪ ሙሉ ይሸፈናል፣

1.25. ሆኖም ከላይ 1/1.23 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ህመሙ ካደረሰበት ጉዳት አንፃር ተገልጋዩ ከሆስፒታል መውጣቱ ለህይወቱ አስጊ ሆኖ ከተገኘና በህክምና ባለሙያ በማስረጃ ተደግፎ ሲገለፅ ከአንድ ወር በላይ እስከ ሶስት ወራት ለሚደርስ ጊዜ በደንበኛው የህክምና ተቋም ብቻ የሚተኛ ታካሚ ወጪው በባለስልጣን መ/ቤቱ ሊሸፈን የሚችለው 50% በአንድ በጀት ዓመት ለአንድ ጊዜ ብቻ ይሆናል፣

1.26. ከላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በመንግስት ሆስፒታል ከአንድ ወር በላይ እስከ ሶስት ወራት ለሚደርስ ጊዜ ተኝቶ ለሚታከም በባለስልጣን መ/ቤቱ ሊሸፈን የሚችለው ወጪ 70% በአንድ በጀት ዓመት ለአንድ ጊዜ ብቻ ይሆናል፣

1.27. ከላይ በአንቀጽ 1/1.22 ያለው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊና ሠራተኛ በደንበኛው የህክምና ተቋምም ሆነ በመንግስት ሆስፒታል ተኝቶ መታከም የሚችለው የአልጋ ማዕረግ ሁለተኛና ከዚያ በታች ብቻ ይሆናል፣

1.28. በሥራ ላይ እያሉ በድንገተኛ አደጋ ለሚደርስ ህመም ማለትም የመኪና፣ የኤሌክትሪክ አደጋ ወዘተ ባለስልጣን መ/ቤቱ ሙሉ የህክምና ወጪ ይሸፍናል፣

1.29. የባለስልጣን መ/ቤቱ ግዴታና ኃላፊነት ህመም ባጋጠመ ወቅት ሠራተኛውን ማሳከም እንጂ ከህመም ውጭ አጠቃላይ ምርመራ/የሜዲካል ምርመራ (Medical Check up) ማድረግ የማይቻል ሆኖ ከህመሙ ጋር ሳይያያዝ አጠቃላይ ምርመራ ያደረገ ሠራተኛ ወጪውን በራሱ የሚሸፍንና ይህ ማዘዣ የሰጠ የባለስልጣን መ/ቤቱ የክሊኒክ ባለሙያ በዲስፕሊን የሚቀጣ ይሆናል፣

1.30. በባለስልጣን መ/ቤቱ ለስልጠና ወደ ውጭ ሀገር ለሚሄዱ ባለሙያዎችና ኃላፊዎች በኤምባሲዎች የሜዲካል ማስረጃ እንዲያቀርቡ ሲጠየቁ ከባለስልጣን መ/ቤቱ የስልጠና ማዕከል ሚረጋገጫ ሲያቀርቡ ላገኙት የስልጠና እድል በደንበኛው የህክምና ተቋም እንዲስተናገዱ ይደረጋል ለዚህም ሙሉ ወጪው ይሸፈናል፣

1.31. ተገልጋዩ በመንግስት ሆስፒታሎች ክትትልና ተኝቶ ህክምና ማድረግ የሚችለው በመጀመሪያ ከመ/ቤቱ ክሊኒክ ወይም ከደንበኛ የግል የህክምና ተቋም ወደ መንግስት ሆስፒታል ሪፈር ተብሎ በክሊኒኩ ካርድ ላይ ሲገለፅ ብቻ ይሆናል፤ ከህክምናው በኋላም ሪፈር የተባለበትን የህክምና ማስረጃ፣ የህክምና አገልግሎቱን ካገኘበት የመንግስት ሆስፒታል ስለመታከሙ/ሟ የሚገልጽ ማስረጃና ሌሎች የምርመራ ማዘዣዎች ከህጋዊ ደረሰኝ ጋር ተያይዞ ሲቀርብ ለህክምናና ያወጡት ወጪ ይተካላቸዋል፣ ሆኖም ግን መድሃኒት ሲታዘዝና ህጋዊ የሐኪም ማዘዣ ይዘው ሲቀርቡ ወል በተገባባቸው የደንበኛ መድሃኒት ቤቶች መድሃኒቶችን እንዲያገኙ ይደረጋል፣

1.32. የኩላሊት ህመም ያጋጠመውና ኩላሊቱ ሙሉበሙሉ የማይሰራ/የደከመ እጥበትና ንቅለ-ተከላን ለማድረግ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅና በተለይ እጥበቱ በየጊዜው በመሆኑ ወጪውን ለመሸፈን ባለስልጣን መ/ቤቱ መንግስታዊ ተቋምና የሚመደብለት በጀት ወስን በመሆኑ ከመንግስት የህክምና ተቋም ብቻ ለሚገኝ የእጥበቱን አገልግሎት ወጪ 50% ሀያ ጊዜ የሚሸፈን ሆኖ ንቅለ-ተከላውን ግን አያካትትም፡

1.33. ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጪ ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ በበዓላት ቀናት በድንገተኛ የታመመና በደንበኛው የህክምና ተቋም ከህመሙ ጋር በተያያዘ በአስቸኳይ እንዲተኛ የተደረገ ሠራተኛ በመደበኛ የሥራ ሰዓት ሰኞ ወዲያው ለተቋሙ ክሊኒክ ደውሎ ማሳወቅ ያለበት ሆኖ ተኝቶ የመታከሙ ሁኔታ በአንቀጽ 1/1.22 መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፣

1.34. የሠራተኛውን ደህንነትና ጤንነት በተገቢው መንገድ በማጠበቅ፣ በሠራተኛው መካካል ስለባለስልጣን መ/ቤቱ የተቆርቋሪነትና የእኔነት መንፈስን ለማስደግ እንዲሁም ውጤታማ ሠራተኛ ይዞ ለመቀጠል ለሴት ሠራተኞች በበጀት ዓመቱ ወስጥ የማህፀን በር ካንሰርና የጡት ምርመራ እንዲሁም ለወንድ ሠራተኞች የፕሮቴስት እጢ ካንሰር ምርመራ ፕሮግራም በማውጣት ይከናወናል፣

1.35. በሀገር ደረጃ ለሚሳ ወረርሽኝ በሽታ ባለስልጣን መ/ቤቱ ከሌሎች የጤና ተቋማት ጋር በመሆን የክትባት አገልግሎት ይሰጣል፣

1.36. የሄፓታይተስ «ቢ» ወይም «ሲ» ቫይረስ ህክምናን በግላቸው ገዝተው ለሚታከሙ ተገልጋዮች ያወጡትን ወጪ 40% ብቻ እንዲሸፈንላቸው ይደረጋል፤ ሆኖም ግን የሄፓታይተስ «ቢ» ቫይረስ ስርጭትን በመካላከል ደህንነቱና ጤንነቱ የተጠበቀ ሠራተኛ እንዲኖር ከማስቻል አንፃር እንደአስፈላጊነቱ ክትባቱን ለተገልጋዮች በባለስልጣን መ/ቤቱ ክሊኒክ በኩል እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ-2

## በቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚገኙ ሠራተኞች የህክምና አገልግሎት አሰጣጥ

ተቋሙ በተለያዩ ክልሎች የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ያለው በመሆኑ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተቀጥረው በቋሚነት/በኮንትራት የሚያገለግሉ ሠራተኞች የህክምና አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ምቹ የሥራ አካባቢን በመፍጠር ሠራተኞቹን ወጥታማ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ለሚገኙ ሠራተኞች የሚሰጠው የህክምና አገልግሎት፡ –

2.1. በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ለሚገኙ ሠራተኞች ለሚደረገው ህክምና የሚሰጠው የህክምናና የመድኃኒት አቅራቢ የአገልግሎት ግዥ አፈፃፀም ሥር□ትን በመከተል ሆኖ በዋናው መ/ቤት የክሊኒክ ባለሙያዎች ድጋፍና ክትትል ይከናወናል፣

2.2. በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ያሉ ተወካዩች/ኃላፊዎች ባሉበት አካባቢ ባሉ መንግስታዊና ህጋዊ ፈቃድ ባላቸው የግል የህክምና ተቋማትና መድኃኒት ቤቶች ጥራቱ የተጠበቀ፣ ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ የሆነ የዱቤ የህክምና አገልግሎት አወዳድሮ ውል በባለስልጣን መ/ቤቱ ስም በመዋዋል አገልግሎቱን ይጠቀማሉ፣

2.3. ተገልጋይ ውል ወደ ተገባበት ደምበኛ የህክምና ተቋማት በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም በተጠሪው በተፈረመ የህክምና እና የመድኃኒት አገልግሎት መፍቀጃ ቅጽ መሠረት የህክምና አገልግሎት ያገኛል፣

2.4. ተገልጋይ ለህመሙ የታዘዘለትን መድኃኒት ውል ከተገባበት መድኃኒት ቤት በተጻፈለት የመድኃኒት ማዘዣ መሠረት በዱቤ ይገዛል፤ **ሆኖም** ከደንበኛው ፋርማሲ መድኃኒቱ ካልተገኘ መድኃኒቱ አለመኖሩን ከሀለት ደንበኛ መድኃኒት ቤት ምልክት በማስደረግ ከማንኛውም የመንግስት ወይም የግል መድኃኒት መድኃኒት ቤት ይገዛል ያወጣውም ወጪ ይተካለታል፣

2.5. ተገልጋይ እንደ ህመሙ ክብደት በህክምና ባለሙያ ተኝቶ እንዲታከም ሲታዘዝ ለ30 ቀናት አገልግሎቱን እንዲያገኝ ሆኖ የሀያ ቀናት ሙሉ ወጪ እንዲሁም የ10 ቀናት 50% የህክምና ወጪ ብቻ በባለስልጣን መ/ቤቱ ይሸፈናል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ከላይ ከተጠቀሱት ቀናት በላይ ተኝቶ ለሚታከም ታካሚ ወጪው በባለስልጣን መ/ቤቱ አይሸፈንም፡፡ ተገልጋዩ ተኝቶ እንዲታከም ሲታዘዝ የአልጋ ማዕረግ ሁለተኛ ከዚያ በታች መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በቅድሚያ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤት ራሱ/ተወካዩ በቅድሚያ ማሳወቅ ይጠበቅበታል፡ ፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ከህክምናው ጋር በተያያዘ የመድኃኒት ግዥ የሚፈፀመው ውል በተገባበት የደንበኛው ክሊኒክ መድኃኒት ቤት ብቻ ነው ይሆናል፣

2.6. በአንቀጽ 1/1.22 እንዲሁም 1.23 እና 1.24 የተገለፀው በክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተፈፃሚ ይሆናል፣

2.7. በቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚገኙ ተገልጋዮች በፈቃድና በልዩ ልዩ ምክንያት ወደ ዋናው መ/ቤት ሲመጡ በባለስልጣን መ/ቤቱ ክሊኒክ የህክምና አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ፤ ከባለስልጣን መ/ቤቱ ክሊኒክ ወይም ከቅርንጫፍ ደምበኛ የህክምና ተቋም ወይም የመንግስት ሆስፒታል ተገልጋዩ ሪፈር ከተባለ ወደ ባለስልጣን

መ/ቤቱ ክሊኒክ በመቅረብ ሪፈር ተጽፎላቸው ባለስልጣን መ/ቤቱ ስምምነት በገባው የህክምና ተቋም አገልግሎቱን እንዲያገኙ ይደረጋል፣

2.8. ከጎዴና ከጋምቤላ ከሚማጡ ተገልጋዮች በስተቀር ማለትም ለቀዶጥገና ወይም ከፍተኛ ድንገተኛ አደጋ ሲያጋጥም ለተገልጋዩ የትራንስፖርት ሂሳብ የሚወራረደው ታካሚው ከማግስት ወይም ከደንበኛ ክሊኒክ ሪፈር የተባሉትን የህክምና ማስረጃና የትራንስፖርት የከፈሉበትን ህጋዊ ደረሰኝ፣ እንዲሁም በከፍተኛ ድንገተኛ አደጋ ምክንያት ለሚማጡ አደጋው በድንገት የደረሰ ስለመሆኑ የሚገልጽ ከቅርንጫፉ ጽ/ቤት ኃላፊ/ተጠሪ በፅሑፍ ቀርቦና በባለስልጣን መ/ቤቱ የክሊኒክ ባለሙያዎች ሲረጋገጫ ሰሰጥ ብቻ ነው፣

2.9. ለከፍተኛ ህክምና ሪፈር ተብሎ ከጎደና ከጋምቤላ የሚማጡ ተገልጋዮች የትራንስፖርት ወጪ የሚሸፈነው ከጎዴ ወደ ድሬዳዋ በአይሮፕላን ከድሬዳዋ ወደ ደንበኛው የጤና ተቋም የሚደረገው ጉዞ በባቡር ወይም በመኪና በመሆኑ ለአወሮፕላን፣ ለባቡር ወይም የተሽከርካሪ ትራንስፖርት ህጋዊ ደረሰኝ ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፣

2.10. አንቀጽ 2/2.8 እንደተጠበቀ ሆኖ ካጋጠመው የጤና ችግር ምክንያት ወደ አዲስአበባ ወይም ክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በሚገኙ የጤና ተቋማት ለህክምና ሪፈር የተላከና ፈፅሞ በተሽከርካሪ መምጣት የማይችል ስለመሆኑ በህክምና ባለሙያዎች የተረጋገጠ ማስረጃ ተያይዞ ሲቀርብ በአወሮፕላን የመጣበት ትኬት ዋጋ እንዲወራረድ ይደረጋል፤ ሆኖም ተጠቃሹ በዚህ ሚልኩ ሊጠቀም የሚችለው በዓመት ሶስት ጊዜ ብቻ ይሆናል፣

2.11. ለከፍተኛ ህክምና ሪፈር ተብሎ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወደ ዋናው መ/ቤት (አ/አ) ደንበኛ የጤና ተቋማት የሚላክ ተገልጋይ የትራንስፖርት ወጪ ከራሱ ይጠቀሜል፡፡ ተገልጋዩ ያወጣውን የትራንስፖርት ወጪ ህጋዊ ደረሰኝ በማቅረብ በሁለት ቀናት እንዲተካ ሲደረግ ነው፣

2.12. የህክምና አገልግሎት ወል ስምምነት ያልተገባላቸውና አነስተኛ የኤርናቪጌሽን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ጅግጅጋ፣ አዋሳ፣ አሶሳ፣ ኮምቦልቻ፣ ደንቢዶሎ፣ ሁሜራ፣ ጎሬ፣ ደብረማርቆስ፣ አርባምንጭ፣ ጎዴ፣ ጋምቤላ፣ ባሌ ሮቤ፣ ሽሬ፣ ጂንካና ሌሎች ወደፊት ሊከፈቱ የሚችሉ ተገቢውን ባለሙያ አሟልተው እስኪይዙ ድረስ ቢቻል በአቅራቢያው ባለው የመንግስት የጤና ተቋም ካልሆነ ህጋዊ እውቅና በክልሉ ጤና ቢሮ በተሰጣቸው የግል የጤና ተቋማት በመታከም የተሟላ ማስረጃ በማቅረብ ክፍያው የሚተካ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ታካሚው ተኝቶ የሚታከም ከሆነ በመጨረሻው በተገለፀው መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ይሁን እንጅ ለህክምና ያወጡት ወጪ የሚተካው ህጋዊ ደረሰኝ፣ ህክምና ስለማግኘታቸው የሚገልጽ በህክምና ባለሙያ የተረጋገጠና ህጋዊ ማህተም ያረፈበት የህክምና ማስረጃ ከመድሃኒትና ከሌሎች የምርመራ ማዘዣዎች ጋር ተያይዞ ሲቀርብ ነው፣

2.13. በክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚገኝ የደንበኛ የህክምና ተቋማት የአገልግሎት ወል የሚራዘመው ከዋናው መ/ቤት የጤና ባለሙያዎች የክትትል ተግባራት ከፈፀሙ በኃላ ነው፡፡

## አንቀጽ -3

### የተቋሙመብትናግዴታ

3.1. ባለስልጣን መ/ቤቱ በማግስትና የግል የጤና ተቋማት በአገልግሎት ግዥ አወዳደሮ ስምምነት በመግባት የሠራተኞችን ደህንነትና ጤንነት ማጠበቅ አለበት፣

3.2. የባለስልጣን መ/ቤቱ ክሊኒክ የሚሰጠውን የህክምና አገልግሎት በማሻሻል አጠቃላይ ሀኪም ወይም ስፔሻሊስቶች በኮንትራት ወይም በቋሚነት በመቅጠር እና ባለሙያዎች ባላቸው አቅም አገልግሎቱን ለተገልጋዩ እንዲሰጡ ሟሟላት የሚገባው የላብራቶሪ እና ሌሎች የመመርመሪያ መሣሪያዎችን፣ ሪኤጀንቶችን፣ ኪቶችን፣

መድኃኒቶችንና ተያያዥ አስፈላጊ ቁሳቁሶችን በማቅረብ ተገልጋዩ በሌላ የደንበኛ የህክምና ተቋማት የሚያገኘውን አገልግሎት በማስጠት ወጪ መቀነስ ይገባዋል፣

3.3. በደንበኛው የህክምና ተቋም ለህክምና የተላከ ተገልጋይ አልጋ ይዞ እንዲታከም በህክምና ባለሙያ ሲወሰን ተኝቶ መታከም የሚችለው ህክምና ተቋሙ የወሰነበት ማስረጃ ተያይዞ ሲቀርብ ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ተኝቶ እንዲታከም የተደረገ ተገልጋይ በ72 ሰዓት ወስጥ በስልክ ወይም ተወካይ በማላክ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፤ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ባለስልጣን መ/ቤቱ ወጪው የሚሸፈን ከመሆኑም በላይ በሥራ ላይ ላልነበሩበት ጊዜ ደመወዝ ተመላሽ ይደረጋል፣

3.4. በሸፍት የሚሰሩ ተገልጋዮች ተረኛ በሆኑበት ዕለት በድንገተኛ ህመም እንደደም ግፊት፣ የስኳር በሽታ፣ አስም እና ተገልጋዩን ለከፍተኛ የጤንነት ችግር የሚያደርሰው ህመም ሲያጋጥም ተገልጋዩ አገልግሎቱን በደንበኛው የህክምና ተቋም ለማግኘት እንዲችል ባለስልጣን መ/ቤቱ ተሽከርካሪ ማቅረብ አለበት፣

3.5. ባለስልጣን መ/ቤቱ በደንበኛው የጤና ተቋም ለሚሰጠው ህክምና የቅድሚያ ክፍያ አይፈፅምም፤ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ተገልጋዩ በመንግስት ሆስፒታል ብቻ ተኝቶ እንዲታከም በህክምና ባለሙያ ሲታዘዝ ተኝቶ እንዲታከም የተሰጠ የህክምና ማስረጃ ቀርቦ በባለስልጣን መ/ቤቱ የህክምና ባለሙያ ሲረጋገጥ የተጠየቀውን ክፍያ የሚፈፀም ሲሆን ይህንን ለሚፈፀም ታካሚው የማሳወቅ ግዴታ አለበት፣

3.6. የባለስልጣን መ/ቤቱ ክሊኒክ በበጀት ዓመቱ ለተገልጋዩ የተፈቀደውን የህክምና በጀት፣ ለመድኃኒትና ለህክምና አገልግሎት ክፍያ የተፈፀመበትን ሂሳብ መዝገብ ይይዛል፣ ለጤና ተቋማቱ የሚከፈለውን ክፍያ ከተያዘው የበጀት ርዕስ እንዲከፈል ያደርጋል፣ ወጪው ከተፈቀደው በጀት በላይ እንዳይሆን ይቆጣጠራል፣

3.7. ከጤና ተቋማት የሚላኩ የህክምና ሂሳብ ማጠየቂያዎች አግባብ ባለው ባለስልጣን ሚዲረሜን፣ ታካሚዎች/ተገልጋዮች የተቋሙ ቋሚ ሠራተኞች መሆናቸው በሰው ሀብት በኩል ሚረጋገጫ ሰስጥ በባለስልጣን መ/ቤቱ የክሊኒክ ባለሙያ ብቻ ተረጋግጦ ክፍያ እንዲፈፀም ያደርጋል፣

3.8. የባለስልጣን መ/ቤቱ ክሊኒክ በዓመት ለህክምናና ለመድኃኒት መግዣ የሚውል በጀትን ያቅዳል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል እንዲሁም ሪፖርት ያደርጋል፡፡

## አንቀፅ - 4

## የተገልጋይ መብትና ግዴታ

4.1. ተገልጋዩ በዋናው መ/ቤት ክሊኒክ፣ በደንበኛው የህክምና ተቋም እንዲሁም በድንገተኛ ህመም ባጋጠመበት ወቅትም ሆነ የህክምና አገልግሎት ሲያገኝ የተሰጠውን የህመም ፈቃድ/Sickleave/ ማስረጃ በ72 ሰዓት በቅድሚያ ለቅርብ አለቃ በመቀጠል በክሊኒክ ማስመዝገብና ምልክት ማስደረግ አለበት፤ሆኖም ከተጠቀሰው ሰዓት ውጭ ወይም የህመም ፈቃዱ ከተጠናቀቀ በኃላ የሚቀርብ የህመም ማስረጃ ተቀባይነት የሌለው ከመሆኑም በላይ ታካሚው የህመም ማስረጃ ሳይልክ በስራ ገበታው ላይ ላልነበረበት ቀናት ደመወዝ ተመላሽ ይደረጋል፣

4.2. ከድንገተኛ ህመም በስተቀር በመደበኛ የሥራ ሰዓትና ቀናት በክሊኒኩ መታከም እየተቻለ በሌሎች ደንበኛ ባልሆኑ የግልና የመንግስት የህክምና ተቋማት ህክምና በማድረግ የሚላክ የህክምና ማስረጃ ተቀባይነት የሚኖረው በክሊኒኩ ባለሙያ ሲታመንበት ብቻ ይሆናል፣

4.3. በደንበኛው የህክምና ተቋም ተኝቶ እንዲታከም የተወሰነለት ተገልጋይ ባገኘው መንገኛ ዘዴ በመጠቀም በ72 ሰዓት ወስጥ ለክሊኒክ ወይም ለሰው ሀብት የማሳወቅ ግዴታ አለበት፤ ይህ ባልተደረገበት ሁኔታ የሚቀርብ የህክምና ወጪ ክፍያ ተቀባይነት አይኖረውም፤ የህክምና ወጪውንም ራሱ ይሸፍናል፣

4.4. ተገልጋዮች በአንቀጽ 1 የተዘረዘሩትን የህክምና አገልግሎት ሙሉ በሙሉ የማግኘት መብት አላቸው፣

4.5. ተገልጋይ ወል በተገባባቸው የጤና ተቋማት የህክምና አገልግሎት ማግኘት የሚችለው በዱቤ ብቻ ነው፤ ስለሆነም በማንኛውም ምክንያት በደንበኛ የህክምና ተቋማት በግል ህክምና አግኝተናል ያወጣነው ወጪ ይተካልን ተብሎ የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡ ከሥራ ሰዓት ውጪ በበዓል ቀናት ካልሆነ በስተቀር ከባለስልጣን መ/ቤቱ ክሊኒክ የህክምናና የመድኃኒት ማዘዣ ፎርም ወይም መሸኛ ሳይዝ አገልግሎቱን ማግኘት አይችልም፤ አንድ የህክምና መላኪያ ፎርም የሚያገለግለው ለተላከበት (ለአንድ) የህክምና ዓይነትና ሐኪም ብቻ ነው፣

4.6. በባለስልጣን መ/ቤቱ ክሊኒክ ባለሙያዎች ወይም በደምበኛ ተቋማት የህክምና ባለሙያዎች የህክምናና የመድኃኒት አገልግሎት ወል በተገባባቸው በደንበኛ የህክምና ተቋማት አገልግሎቱን እንዲያገኝ በተጻፈለት የመድኃኒት ማዘዣና የህክምና ሪፈር ላይ በራሱ ፍላጎት ዓይነትን፣ ማጠንን፣ ቀንና የተጻፈን ነገር አስተካክሎ አገልግሎቱን ማግኘት አይችልም፤ ለዚህም የህክምና ወጪዎን ራሱ እንዲከፍል ይደረጋል፣ በዲስፒሊንም ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## አንቀፅ - 5

## የመድኃኒት ግዥ አገልግሎት

5.1. የባለስልጣን መ/ቤቱ ክሊኒክ መድኃኒት ቤት በተቻለ መጠኑ ተገልጋዩ የሚጠቀምባትን መድኃኒቶችን አሟልቶ ይይዛል፣

5.2. የክሊኒኩ መድኃኒት ቤት በተቻለ መጠን በደረጃው ሊያዙ የሚችሉ በወስጥ ክሊኒክና በውጭ የደምበኛ የህክምና ተቋማት ለተገልጋይ የሚታዘዙ መድኃቶችን ይይዛል፣ የሌሉ መድኃኒቶችን በደምበኛ መድኃኒት ቤት እንዲያገኙ ያደርጋል፣

5.3. ባለስልጣን መ/ቤቱ ከመንግስት የመድኃኒት አቅራቢ መድኃኒቶችን ለማስገባት የዱቤ መድኃኒት ወል ስምምነት ይፈፅማል፣ ከግል መድኃኒት አምራችና አቅራቢ ድርጅቶች ጥራት ያለው መድኃኒት በተሟላ መልኩ ሠራተኛው በማግኘት ተጠቃሚ እንዲሆን በግልፅ አወዳድሮ ይገዛል፣

5.4. የባለስልጣን መ/ቤቱ ሠራተኞች በቅድሚያ የታዘዘላቸውን መድኃኒት በክሊኒኩ መድኃኒት ቤት ያለመኖሩ ማረጋገጫ ሰጥቶ የዱቤ መድኃኒት አገልግሎት ለማቅረብ ወል ከተገባባት መድኃኒት ቤቶች አገልግሎቱን ያገኛሉ፣

5.5. የባለስልጣን መ/ቤቱ ሠራተኞች የዱቤ መድኃኒት ከሚቀርበው ደንበኛ መድኃኒት ቤት የታዘዘው መድኃኒት ካላገኙ መድኃኒቱ ያለማግኘቱን የሚገልጽ ምልክትና ማህተም ቢያንስ ከሁለት መድኃኒት ቤቶች በማስደረግ በመንግስት ህጋዊ እውቅና ከተሰጠው የመድኃኒት አቅራቢ ማእትም ከቀይ መስቀል፣ ከመንግስት መድኃኒት ቤቶች ወይም ከግል መድኃኒት ቤት ይገዛል፡፡

## አንቀፅ - 6

## የድንገተኛ የህክምና አገልግሎት አሰጣጥ

ድንገተኛ ህመም ማለት የተገልጋዩ የህመም ሁኔታ ጊዜ የሚሰጥና ወዲያው የህክምና እርዳታ ካላገኘ በህይወትና በአካል ላይ ከፍተኛ እና ዘላቂ ጉዳት ወይም አደጋ ሊያደርስ የሚችል ህመም ሲሆን፡ -

6.1. አንድ ሠራተኛ ከሥራ ሰዓት ውጭ፣ በበዓላት ቀንና ቅዳሜ እሁድን ጨምሮ ድንገተኛ ህመም ካጋጠመው ያለ ሪፈራል ወረቀት የባለስልጣን መ/ቤቱ ማታወቂያ በማሳየትና ኮፒውን በማያያዝ ብቻ ወል ከተገባበት ደንበኛ የህክምና ተቋም ወይም በማንኛውም የመንግስት ጤና ተቋማት ህክምና ሊያገኝ ይችላል፣

6.2. በድንገተኛ ህመም ምክንያት ደንበኛ ካልሆነ የመንግስትና የግል የህክምና ተቋም የህክምና አገልግሎት ያገኘ ተገልጋይ በዕለቱ የመጀመሪያ እርዳታ ላገኘበት የህክምናው የጠቅላላ ወጪ 100% ይሸፈናል፡፡ ሆኖም የመጀመሪያ እርዳታ በድንገተኛ ህመም ምክንያት ካገኘ በኃላ ወዲያውኑ ወደ ደንበኛው የጤና የህክምና ተቋም ቀጣይ ህክምናውን ማግኘት ይገባዋል፣

6.3. ከላይ አንቀጽ 6/6.2 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በመንግስት ሆስፒታል አገልግሎቱን አግኝቶ ቀጣይ ህክምናውንም በመንግስት ሆስፒታሉ የሚቀጥል ከሆነ ባለስልጣን መ/ቤቱ እስከ ሀያ ቀናት ድረስ ያለውን ሙሉ ወጪ ይሸፍናል፣

6.4. አንቀፅ 6/6.2 እንደተጠበቀ ሆኖ ተገልጋዩ በሥራ ገበታው ላይ እያለ የመኪና አደጋ ወይም የእሳት ቃጠሎና ተመሳሳይ ድንገተኛ አደጋ ቢደርስበት አደጋው ጊዜ ስለሚዩሰጥ ደንበኛ ባልሆነ የህክምና ተቋም ላገኘው የመጀመሪያ እርዳታ አገልግሎት ሙሉ ወጪ ይሸፈናል፡፡

6.5. በድንገተኛ አደጋ (የእሳት፣ የተሽከርካሪ፣ውሃ የመሳሰሉት) ሳቢያ በደንበኛ ባልሆነ የህክምና ተቋም አገልግሎት ያገኘ ተገልጋይ የታዘዘውን መድኃኒት የዱቤ ማጠየቂያ ደብዳቤ ከባለስልጣን መ/ቤቱ ክሊኒክ መውሰድ ሳያስፈልገው በመታወቂያው በቅድሚያ ከደንበኛ መድኃኒት ቤት መድኃኒቱን ይወስዳል ካልተገኘ ከሌላ ፋርማሲ ገዝቶ ይጠቀማል፣

6.6. ተገልጋዩ በሥራ ጉዳይ ወደ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተልኮ በድንገት ቢታመም ደንበኛ የህክምና ተቋማት ባላቸው ቅርንጫፎች በዚያው ህክምናውንና የመድኃኒት ቤት አገልግሎትን ያገኛል፤ ሆኖም ግን ደንበኛ የህክምና ተቋማት በሌለበት አካባቢና በአረፍት ላይ ከአዲስ አበባ ወጪ ማለትም በሌሎች በኢትዮጵያ ክልሎች እያለ ቢታመም በተገኘው የመንግስት ወይም የግል የህክምና ተቋም አግኝቶ የተሟላ የህክምና ማስረጃና ማዝዣዎችን ከየክፍያ ሰነድ ጋር አያይዞ ሲያቀርብ ያወጣው ወጪ ይተካል፣

6.7. ተገልጋዩ በሥራ ላይ ለሚደርስበት ድንገተኛ አደጋ ከደንበኛ የጤና ተቋማት አቅም በላይ ሆኖ ሲገኝ በሀገር ወስጥ ካሉ ሌሎች የጤና ተቋማት የህክምናው ሙሉ ወጪ ተሸፍኖ ማግኘቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ከደረሰበት አደጋ አንፃር በመተኛት ህክምና ማግኘት ካለበት አንቀጽ 1/1.22 መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፣

6.8. በሀገር ወስጥ ባሉ የህክምና ተቋማት አቅም በላይ የሆነ ህመም ላጋጠማቸውና ከኢትዮጵያ ወጪ እንዲታከሙ ሪፈር የተደረጉ ሠራተኞች ህክምና ወጪ በተቋሙ አይሸፍንም፡፡

6.9. በድንገተኛ ህመም ሳቢያ የሚቀርቡ የህክምና እረፍት ማስረጃዎች (ሲክሊቭ) በባለስልጣን መ/ቤቱ የክሊኒክ ባለሙያዎች እንደ ህመሙ ዓይነት ታይቶ በድንገተኛ የሚያሳክም ህመም መሆኑን ሚረጋገጫ ሲሰጡ ብቻ ተቀባይነት ይኖረዋል፣

## አንቀፅ - 7

## የህክምና አገልግሎት የክፍያ አፈፃፀም

7.1. የተቋሙ ሠራተኞች ከደንበኛ የህክምና ተቋማት እና በግላቸው ለሚያገኙት የህክምና አገልግሎት የቅድሚያ ክፍያ አይፈፀምም፡፡

7.2. የህክምና ተቋማት ለሠራተኞች ለሰጡት አገልግሎት በመዉያወና በወል ስምምነት መሠረት ህጋዊ የክፍያ ሰነድ ከተሰጠው የህክምና ምርመራ ዓይነት ጋር በዝርዝር አያይዘው ሲያቀርቡ ክፍያ ይፈፀማል፣

7.3. ታካሚዎች ከደንበኛ መድኃኒት ቤት የታዘዘወን መድኃኒት ሲያጡ በመሚያው አንቀፅ 5/5.5 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ተሟልቶ በሚቀርበው ህጋዊ የክፍያ ሰነድ መሠረት በተቋሙ የክሊኒክ ባለሙያዎች ሲረጋገጥ ብቻ ክፍያው ይተካላቸዋል፣

7.4. የድንገተኛ ህመም/አደጋ የደረሰበት ታካሚ አንቀፅ 6/6.4 እንደተጠበቀ ሆኖ የታዘዘወን መድኃኒት ደንበኛ ካልሆነ የህክምና ተቋም ሲገዙ ወጪው ሊተካ የሚችለው የመድኃኒት ማዝዣው ከህጋዊ የክፍያ ሰነድ ጋር ተያይዞና ስለህመሙ ድንገተኛነት/ወዲያው መድኃኒቱን/ተገዝቶ ተገልጋዩ መወሰድ/ማጠቀም እንደሚገባው በባለስልጣን መ/ቤቱ ባለሙያዎች ወይም ከደንበኛው የጤና ተቋም ተረጋግጦ ሲቀርብ ብቻ ነው፣

7.5. የባለስልጣን መ/ቤቱ ሠራተኞች ካጋጠማቸው ህመም አንፃር የታዘዘላቸወን ምርመራ በደንበኛው የህክምና ተቋም ለማግኘት ካልቻሉ፣ የደንበኛው የህክምና ተቋም ወደ ሌላ የህክምና ተቋም ሪፈር ሲደረጉ ብቻና ሪፈር ከተደረጉበት የህክምና ተቋም በራሳቸው ወጪ የምርመራ አገልግሎቱን ላገኙበት ከመንግስት ሆስፒታል ከሆነ የወጪ 100% የሚተካ ሲሆን የግል የጤና ተቋም ከሆነ የወጪ 50% ብቻ በተቋሙ ይሸፍናል፣

7.6. ከላይ በአንቀጽ 7/7.5 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከደንበኛ የህክምና ተቋማት ሠራተኛው ካጋጠመው ከፍተኛ የጤንነት እክል ምክንያት በስፔሻሊስቶች መታየትና ተኝቶ ክትትል መደረግ እንዳለበት በደንበኛው የህክምና ተቋም ሲረጋገጥና በሪፈር ማንግስታዊ ሆስፒታል ተኝቶ ለሚታከምበት ከሆነ ሙሉ ወጪ የሚሸፈን ሲሆን፤ ተኝቶ መታከም የሚችለው ደንበኛ ባልሆነ የግል ሆስፒታል ከሆነ በመሚያው አንቀጽ 1/1.22 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የአልጋ ወጪ 40% ብቻ እንዲተካ ይደረጋል፣

7.7. በደምጠኛ የህክምና ተቋማትና በግል ለህክምና ከሚወጣው የህክምና ወጪ ላይ ከካርድ ወጪ 10% እንዲሁም ከላብራቶሪ ምርመራ ወጪ 10% ተገልጋዩ ይችላል፣ ይህም ከደመወዝ ላይ ተቆራጭ ይደረጋል፡፡

## አንቀፅ - 8

## ከህክምና ተቋማት ጋር ውል ስለመዋዋል

8.1. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለመድኃኒት አቅርቦት፣ ለህክምና አገልግሎትና ለዲያግኖሲንግ ምርመራ ማዕከሎች ስምምነት በገባባቸው የህክምና ተቋማትና መድኃኒት ቤቶች የወል እድሳት የሚደረገው በየሁለት ዓመት ሲሆን ይህ የሚሆነው የክትትል/Supervision/ ሥራ ተከናውኖ በክሊኒካችን የህክምና ባለሙያዎች እውቅና ሲሰጥና ሲረጋገጥ ብቻ ነው፣

8.2. በአንቀፅ 8/8.1 ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ስምምነት የተገባባቸው የህክምና ተቋማትና መድኃኒት ቤቶች በስምምነቱ ዘመን የሰጡትን ዋጋ እንደሀገር የዶላር ምንዛሬ ለውጥ ካልተደረገ ወይም ሌሎች አሳማኝ ምክንያቶች ካልቀረቡ በቀር ማለወጥ አይችሉም፣

8.3. የወሉ ዘመን ሲያበቃ የጤና ተቋማቱ በተለያየ ምክንያት ለሚጠቱ የህክምና አገልግሎት ዋጋ ቢጨምሩ የአቻ **የህክምና** ተቋማት የአገልግሎት ጥራትና የገበያ ዋጋ በማጥናት በቀጣዩ የወል ዘመን አዋጪ ሆኖ ሲገኝ ወሉ ሊራዘም ይችላል፣

8.4. የደንበኛ **የህክምና ተቋ**ማት የአሰራር ሥር□ቱን ተከትለው በሪፈር ለህክምና የሚጡ ተገልጋዮች በትክክል ሪፈር ስለመደረጋቸው የሚገልፅ ማስረጃ ማቅረባቸወን በሚጋገጥ እና በተፃፈላቸው የሪፈር ዓይነት (ስፔሻሊቲ) ብቻ ህክምናወን ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ-9

## የህክምና ተቋማትን ስለመምረጥ

9.1. ማንኛውም የህክምና ተቋም እና የመድኃኒት ቤቶች አገልግሎት እንዲሰጡ የሚደረገው በአገልግሎት ግዥ በጨረታ ወድድር ተመርቶ ነው፣ ሆኖም ግን በዳቤ የሚሰጡ የመንግስት ሆስፒታሎችንና መድኃኒት ቤቶች ያለ ጨረታ በደንበኝነት እንዲካተቱ ይደረጋል፣

9.2. የህክምና እና መድኃኒት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚሰጡትን ህክምና እና የመድኃኒት ዓይነትና ዋጋ ዝርዝር በወል ስምምነቱ ወቅትም ያቀርባሉ፣

9.3. የጤና ተቋማት የሚሰጡትን ዝርዝር ህክምና ከምርመራ ዋጋ ጋር በወድድር ወቅት በሰም በታሸገ ኢንቨሎፕ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፣

9.4. የህክምና ተቋማት የሚሰጡት የህክምና ወል ዋጋ ለአንድ ዓመት የፀና ሆኖ በመጀመሪያው ዓመት የሰጡት ዋጋ በምንም ዓይነት መልኩ አይቀየርም፡፡ ሆኖም የተለየና በመንግስት ታወቆና እንደሀገር የወጭ ምንዛሬ ዋጋ ለወጥ መኖሩ ሲረጋገጥ እና ሌሎች ተጨባጭና አሳማኝ ምክንያቶች ሲቀርቡ አንፃራዊ/ያልተጋነነ የዋጋ ለወጥ የሚደረግ የሚቻል ሲሆን ባለስልጣን መ/ቤቱ ስምምነቱን መቀጠል የሚቻለው የጤና ተቋማቱ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የክትትል ስራ በማከናወንና የተሰጠው ዋጋ ከገበያ ዋጋ ጋር ያለውን ልዩነት በሚፈተሽ ይሆናል፣

9.5. በአገልግሎት ግዥ የሚፈፀም የህክምና አገልግሎት የክሊኒኩ ባለሞያዎች የቴክኒካል መስፈርት ከማዘጋጀት ጀምሮ ባለው የግዥ ሂደት ሁሉ በአባልነት በመሳተፍ ግዥው በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ እንዲፀድቅ ይደረጋል፣

9.6. በክልል ባሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ያለው የህክምና አገልግሎት ግዥ አፈፃፀሙ የዋና መ/ቤት ያለውን ሂደት ተከትሎ በክሊኒኩ ባሉ ባለሞያዎች ድጋፍ ይሆናል፡፡

## አንቀፅ - 10

## የህክምና መመሪያ የተፈፃሚነት ወሰን

10.1. የህክምና መመሪያው የሚያገለግለው በባለስልጣን መ/ቤቱና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በቋሚነት ተቀጣሪ ለሆኑ ሠራተኞች፣ የኮንትራት ተቀጣሪና አዲስ ምልምል ሰልጣኞችን ይሸፍናል፡፡

## አንቀፅ - 11

## የህክምና አገልግሎት ውል ስለማቋረጥ

11.1. ተቋሙ የህክምና አገልግሎት ከሚሰጡ የህክምና ተቋማት ለሠራተኞቹ የተሰጠው አገልግሎት አርኪ አለመሆኑን በክትትል/ሱፐርቪዥን ሲረጋገጥ ወዲያው ወሉን ያቋርጣል፣

11.2. የባለስልጣን መ/ቤቱና የህክምና አገልግሎት ተቋማት በሚገቡት ስምምነት በወል ዘመኑ የሚሰጡ አገልግሎቶች ባለስልጣን መ/ቤቱን ለአላስፈላጊ ወጪ የሚዳርጉት ሲሆንና ወል የተገባባቸው የህክምና ተቋማቱ ከወል ወጪ አገልግሎት እየሰጡ ከሆነ ወሉ በ10 ቀናት ወስጥ እንዲቋረጥ የሚደረግ ሆኖ ከስምምነት ወጪ ለተፈፀመው አገልግሎትም ክፍያ የሚፈፀም ግዴታ ተቋሙ አይኖረውም፡

11.3. የህክምናው ዋጋ ለምን ያህል ጊዜ ፀንቶ እንደሚቆይ በግዥው ወቅት የሚወሰን በመሆኑ የህክምና ተቋማት በወል ዘመኑ ያለተጨባጭ ምክንያትና ያለባለስልጣን መ/ቤቱ ስምምነት የህክምና ዋጋ ከፍ አድርገው ቢገኙ ለሰጡት አገልግሎት ክፍያ አይፈፀምም፡ ወሉም እንዲቋረጥ ይደረጋል፣

11.4. የህክምና ተቋማት በራሳቸው ተቋም ህክምናወን ማድረግ እየቻሉ ያለተጨባጭ ምክንያት ወደ ሌላ ደንበኛ ወደአልሆነ የግል ህክምና ተቋም ሪፈር ማድረጋቸው በማስረጃ ተደግፎ ከቀረበ ተቋሙን ለአላስፈላጊ ወጪ በመዳረጋቸው የወል ስምምነቱ ወዲያው ይቋረጣል፣

11.5. የህክምና ተቋማት አገልግሎቱን ማስጠት የሚችሉት በክሊኒኩ ኃላፊ ቲተር የተመታ የሪፈራል ወረቀት ይዘው ለሚማጡት የባለስልጣን መ/ቤቱ ሠራተኞች ብቻ ሲሆን ከባለስልጣን መ/ቤቱ የህክምና ማዘኛ ሪፈራል ተሰጥቶ የየባስልጣን መ/ቤቱ ሠራተኛ ላልሆነ/ለሠራተኛው ቤተሰብ በሠራተኛው ስም ለሁለተኛ ወገን ህክምናው እንዲሰጥ የጣከረና እንዲሰጥ ያደረገ ኃላፊና የህክምና ባለሙያ እንዲሁም ይህ እንዲፈጸም ጣከራ ያደረገ ሠራተኛ በዲስፒሊን እንዲጠየቅ ተደርጎ ወጪዉም በተቋሙ አይሸፈንም ተጠየቂው ይሸፍናል፣

11.6. በባለስልጣን መ/ቤቱና በህክምና እና በመድኃኒት ቤቶች ተቋማት የሚያጋጥም አለመስማማትና ያለመግባባት በኢትዮጵያ ህግ መሠረት ይፈታሉ፡፡

## አንቀፅ-12

### የተቋሙ ክሊኒክ ባለሙያዎች ግዴታና ኃላፊነት

12.1. የባለስልጣን መ/ቤቱ የህክምና ባለሙያዎች ለተገልጋዩ በቂ የሆነ የህክምና አገልግሎት ማስጠት የሚገባቸው ሆኖ ክሊኒኩ በሥራ ቀናት ለተገልጋዩ ክፍት መሆን ያለበት ሆኖ፤ ስብሰባ ሲያጋጥምና በሻይ ሰዓት ተገልጋዩ አገልግሎት ማጣት የሌለበትና የድንገተኛ ህመም አጋጥሞት የሚመጣ ተገልጋይ አገልግሎቱን ወዲያውኑ የማስጠት ግዴታ አለባቸው፣

12.2. የባለስልጣን መ/ቤቱ የህክምና ባለሙያዎች የህክምና ባለሙያ ሥነ-ምግባርን በመላበስ ለተገልጋዩ በቂ አገልግሎት ማስጠት የሚገባቸው ሆኖ በባለስልጣን መ/ቤቱ ታክሞ ሊድን የሚችል ተገልጋይን ተጨባጭነት በሌለው ምክንያት ወደ በደንበኛው የህክምና ተቋም መላክ የለባቸውም፤ ስለሆነም በትውውቅ በክሊኒኩ መታከም ያለበትን ተገልጋይ ተጨባጭነት በሌለው ምክንያት ተልኮ ቢገኝ ባለሙያው ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ በዲስፒሊን እንዲጠየቅ ይደረጋል፣

12.3. የባለስልጣን መ/ቤቱ የህክምና ባለሙያዎች በደንበኛ የህክምና ተቋማት ስለሚሰጠው አገልግሎት ወል ለሚዘም ተገቢወን የሙያ ዲስፒሊን ጠብቆ የክትትል/የሱፐርቪዥን ሥራ ማከናወን ያለባቸው መሆኑ፣

12.4. የባለስልጣን መ/ቤቱ የህክምና ባለሙያዎች የህክምና አገልግሎት ግዥ ሲፈፀም በሰነድ ዝግጅትና በቴክኒክ ግምገማ ወቅት ሙያዊ እገዛ ማድረግ አለባቸው፣

12.5. የባለስልጣን መ/ቤቱ የህክምና ባለሙያዎች የባለስልጣን መ/ቤቱ የህክምና ወጪ የሚቀንስበትን መንገድ በማጥናት አማራጮችን ያቀርባሉ፤በባለስልጣን መ/ቤቱ የክሊኒክ ደረጃ የሚሰጥ ህክምና በማሟየትና ተገቢው የህክምና መሣሪያ እንዲሟላ በማድረግ ተገልጋዩ ሳይንገላታ አገልግሎቱን እንዲያገኝና በተቋሙ የክሊኒክ ደረጃ የሚሰጥ ማንኛወንም ህክምናን በክሊኒኩ የማስጠት ኃላፊነት አለባቸው፣

12.6. ወል በተገባባቸው የህክምና ተቋማት ለተሰጡት የህክምና አገልግሎቶች ክፍያ እንዲፈጸም ሰነዶች በሚቀርብበት ወቅት ክፍያ ለሚፈጸም እንዲያስችል በህክምና መመሪያውና በወሉ መሠረት ህክምናው ስለመከናወኑ የቀረቡ የህክምና ወጪዎችን ባለሙያዎች በጥንቃቄ ያጣራሉ፣

12.7. የባለስልጣን መ/ቤቱ የህክምና ባለሙያዎች ለታካሚው የሚሰጠው የህክምና ፈቃድ ህመሙን ብቻ መሠረት ያደረገ መሆኑን በማገናዘብ የህክምና ሙያ ሥነ-ምግባርን በጠበቀ መልኩ ማከናወን አለባቸው፤ ከሥራ ሰዓት ውጭና በበዓል ቀናት የመ/ቤቱ ሠራተኞች በክሊኒካችን ሳይላኩ በድንገተኛ ታክመው የህክምና እረፍት (ሲክሊቭ) ይዘው ሲቀርቡ የህክምና ችግሩ በድንገተኛ የሚያሳክም እና አጣዳፊ መሆኑን ብቻ በሚፈተሸ

ሚጋገጫ ያደርጋሉ፣ (በሥራ ቀናት ደንበኛ ባልሆነ የህክምና ተቋም ከድንገተኛ ህክምና ወጪ የሚቀርብ የህማም ፈቃድ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረወም፡

12.8. ክሊኒኩ የታካሚውን የህክምና ታሪክ ሚጃ በማባ ሜራጀትና የህክምና ማስረጃዎችን በዳታቤዝ በማዝ ሪፖርትም በየወቅቱ ያቀርባሉ፣

12.9. የባለስልጣን መ/ቤቱ የህክምና ባለሞያዎች በባለስልጣን መ/ቤቱ አገልግሎት እየሰጠ ያለውን ካፍቴሪያ ሁኔታ በየወቅቱ ይቆጣጠራሉ፣ ሞዋዊ አገዛ ያደርጋሉ እንዲሁም ከጤና ጋር በተያያዘ ባለው ችግር ላይ ጉደለት ከታየና ለማስተካከል ፈቃደኛ ሆነው ካልተገኙ ክትትል በሞድረግ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋሉ፣

12.10. የባለስልጣኑ መ/ቤት የጤና ባለሞያዎች በየወቅቱ የሚከሰቱ በሽታዎች ላይ ቅድመ ጥንቃቄ ለሞድረግ እንዲቻል ለሠራተኛው የጤና ትምህርት/ስልጠና ይሰጣሉ እንዲሁም በተለያየ ዘዴ በማጠቀም ስለሁኔታው ግንዛቤ ያስጨብጣሉ፣

12.11. ማንኛወም ሠራተኛ ተኝቶ እንዲታከም በደንበኛው የጤና ተቋም ሲታዘዝ ባለሞያዎቹ በማከታተል ለህማሙተኛው ድጋፍ ማጠትና ተኝቶ የቆየበትን ጊዜያት የማሳወቅ ኃላፊነት አለባቸው፣

12.12. ከቆዳ ጋር በተያያዘ በክሊኒኩ ደረጃ ባለሞ ባለሞኖሩ በደንበኛው የህክምና ተቋም ካልታዘዘ በቀር የህክምና ባለሞያዎቹ ኮስሞቲክስና ልዩ ልዩ የሚቀዋቢያ ቅባቶች ማዝዝ የለባቸውም፤ ይህ ክልከላ እንዳለ ሆኖ በቸልተኝነት አግባብ ባለው ባለሞ ሳይታዩ በባለሞያዎቹ ታዞ ቢገኝ ባዘዘው ባለሞ ላይ ተገቢው የዲስፒሊን እርምጃ ይወሰዳል፣

12.13. የመ/ቤታችን ክሊኒክ ኃላፊ በክሊኒኩ የሚሰጡ የህክምና አገልግሎቶች በፌደራል የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ቁጥጥር ባለስልጣን ስታንዳርድ መሠረት ህክምናው እየተሰጠ መሆኑን ይከታተላል፣ ባለሞያዎችን በተገቢው የሥራ ክፍል ይመድባል/ያሰራል፣ የታካሚዎች የህክምና እና የወጪ ሚጃዎችን በተገቢው ሜሉኩ እየተማዝገቡ መሆናቸውን ይከታተላል፣ በክሊኒኩ የሚሰጡ አገልግሎቶችን በሙሉ በኃላፊነት ይከታተላል፡፡

## አንቀፅ - 13

### ልዩ ልዩ አፈፃፀም

13.1. ከባለስልጣን መ/ቤቱ ጋር ስምምነት የገባው የህክምና ተቋም ታካሚው ካጋጠመው ህመም አንፃር ተጨማሪ ምርመራ/ህክምና የሚያስፈልገው መሆኑን ካመነ ለታካሚው በቅድሚያ ያሳወቃል፤ ታካሚው የታዘዘለት ምርመራ በደንበኛ የጤና ተቋም የሚሰጥ ከሆነ በዚያው ተቋም ምርመራውን እንዲያገኝ ይደረጋል፤ ሆኖም ግን ምርመራው የሚሰጥ ከሆነ ምርመራው ስላለመደረጉ ማዝዣ ላይ ምልክት አስደርገው ሲቀርቡ በባለስልጣን መ/ቤቱ የክሊኒክ ባለሞያዎች እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡ የታዘዘለት ተጨማሪ ምርመራ/ህክምና በሌላ የደንበኛ የህክምና ተቋም የሚገኝ ከሆነ ታካሚው በደምበኛ የህክምና ተቋም አገልግሎቱን እንዲያገኙ ይደረጋል፣ በደምበኛ የህክምና ተቋም ምርመራው/ህክምናው የሚከናወን ከሆነ ቢያንስ ከሁለት የህክምና ተቋም ህክምናው ያለማኘቱን ምልክት አስደርጎ በግል ተከናወኖ ህጋዊ ደረሰኝ ይዞ ሲመጣ የወጣው ወጪ ይተካል፤ ይህ ካልሆነ ና ህሙሙ ድንገተኛና አጣዳፊ ስለሚሆኑ በባለሞ የተገለፀ ማስረጃ ሲቀርብ የተቋሙ ደንበኛ ባልሆነ ና ሀገር ወስጥ በሚገኝ የህክምና ተቋም የተሰጠውን የህክምና አገልግሎት የምርመራና የአልጋ ወጪ50% ይሸፈናል፣

13.2. በባለስልጣን መ/ቤቱ የክሊኒክ ህክምና ባለሞያዎች የሚሰጠው የህማም ፈቃድ እንደ ህሙሙ ሁኔታና እንደ ባለስልጣን መ/ቤቱ ክሊኒክ ደረጃ ስለህማም ፈቃድ አሰጣጥ በሚወጣው መሜያ ተፈፃሚ ይሆናል፣ ሆኖም

የሚሰጠው የህመም ፈቃድ የህክምና ሞያና ሥነ-ምግባርን መሠረት ያደረገ መሆን ይገባዋል፡፡ በክሊኒኩ ደረጃ ህመሙን መሠረት ባደረገ ሜኪኩ የሚሰጠው የህመም ፈቃድ ሰባት/ ቀናት መብለጥ የለበትም፡

13.3. ታካሚው በባለስልጣን መ/ቤቱ የህክምና ባለሞያዎች ሪፈር ተደርጐ ወደ ተላከበት የጤና ተቋም አገልግሎት እንዲያገኝ የአንድ ቀን ፈቃድ ይሰጠዋል፤ ሆኖም ለዚህ ቀን በህክምና ላይ ስለመሆኑ ከታከሚበት የደንበኛ የህክምና ተቋም ማስረጃ ያቀርባል፡፡

13.4. ከድንገተኛ ህመም በስተቀር ታካሚው በክሊኒኩ ሪፈር ሳይደረግ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆነ የጤና ተቋማት ወጪ ለሚያገኘው የህክምና አገልግሎት ክፍያ ባለስልጣን መ/ቤቱ አይሸፍንም፡

13.5. ታካሚው ከህክምና ተቋማት የተሰጠውን የህክምና ትዕዛዝ ባለማክበር ለሚደርስበት ህመም በህክምና ባለሞያዎች ሲረጋገጥ ተጨማሪ ወጪ ባለስልጣን መ/ቤቱ አይሸፍንም፡ ባለሞያዎችንም ተጠያቂ አያደርግም፡

13.6. በባለስልጣን መ/ቤቱ መደበኛና ዘለቄታዊ በሆኑ ሞያዊ የሥራ መደቦች በቋሚነትና በኮንትራት የሚሰሩ ባለሞያዎች እንዲሁም ከስድስት ወራት በላይ በኮንትራት በሌሎች ሥራ መደብ ለሚቀጠሩ ሠራተኞች በሥራ ላይ ለሚያጋጥማቸው ህመም በባለስልጣን መ/ቤቱ ክሊኒክና በደንበኛው የህክምና ተቋም እንደ ቋሚ ሠራተኞች በዓመት ለህክምና ከሚወጣው ሜክትም በደንበኛው የጤና ተቋም ለካርድ 10% እንዲሁም በየጊዜው ለሚደረግ የላብራቶሪ ምርመራ 10% ከደመወዛቸው ተቆራጭ በሚደረግ የህክምና አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ፣

13.7. ከላይ የተጠቀሰው አንቀጽ 13/13.6 እንደተጠበቀ ሆኖ ከኤች.አይ.ቪ ቫይረስ/ኤድስ ጋር የተያያዘ ለሚደረግ ምርመራ፣ ተኝተው ለሚታከሙ (ከተኙበት ሰዓት ጀምሮ ላለው) እና የእርግዝና ክትትል ለሚከናወኑ ነፍሰጡር ሴት ሠራተኞች ተፈፃሚ ያለመሆኑ፣

13.8. ከላይ የተጠቀሰው አንቀፅ 13/13.6 እንደ ተጠበቀ ሆኖ ከሥራ ጋር በተያያዘ የሚያጋጥማቸው ህመም በባለስልጣኑ መ/ቤት ክሊኒክ እንዲሁም በደንበኛው ተቋም አገልግሎቱን ያገኛሉ፤ ከደንበኛው የመድኃኒት ቤት ለሚወስዱት መድኃኒት ወጪው በተቋሙ ይሸፈናል፣

13.9. በአንቀጽ 1.2፣1.4፣1.9፣4.2 እና 4.5 ከሰፈረው ውጭ ለሚደረግ አገልግሎት አገልግሎቱን ያገኘው ተገልጋይ ወጪውን እንዲሸፍን ይደረጋል፡፡

## አንቀፅ -14

### የተሻሩ የህክምና አገልግሎት መመሪያ

ከዚህ በፊት በሥራ ላይ ወሎ የነበረ የህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ማንዋል/መመሪያና ከመመሪያው ጋር የተያያዙ ዘዋሪ ደብዳቤ፣ልማዳዊ የአሰራር ልምድና ማንኛውም ማበራሪያ ይህ የአሰራር ማንዋል ፀድቆ በሥራ ላይ ከዋለ ጊዜ ጀምሮ ተሽሯል፡፡

## አንቀፅ-15

### መመሪያውን ስለማሻሻል

የህክምና መመሪያው ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ታይቶ ሊያሰራ የሚችል መሆኑ ሲታመንበት በማንኛውም ወቅት ማሻሻል ይቻላል፡፡

## አንቀፅ - 16

### መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ የህክምና አገልግሎት አሰራር ማንዋል ከፀደቀበት ሐምሌ 1 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡